የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ

LISAN HIG GAZETA

OF THE BENISHANGUL — GUMUZ REGIONAL STATE

17 ኛ ዓመት ቁጥር 14 አሶሳ ታህሳስ 1991ዓ/ም

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ

17ተh Year No 14 Assosa December 1999


| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| አዋጅ ቁጥር 14/1991 ዓ.ም | proclamation No 14/1999 |
| የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1991 ሥራዎች የታወጀ የበጀት አዋጅ | Benishangul Gumuz National Regional State Budget proclamation |

## አዋጅ ቁጥር 14/1991

## ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ለ1991 ሥራዎች የታወጀ አዋጅ:

በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊ□ ሕገ መንግስት አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ክልሉ የራሱን በጀት የማቀድና ሥራ ላይ ለማዋል በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ለ1991 የበጀት ዓመት በክልሉ ውስጥ ለሚከናወኑ ሥራዎችና አገልግሎቶች የሚያስፈልገውን በጀት ለበጀት ዓመቱ አጽድቆ ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ በመሆኑ::

## PROCLAMATION NO 14/1999

## BUDGET PROCLAMATION FOR BENISHANGUL GUMUZ REGIONAL GIVERNMNT UNDERTAKINGS

Whereas, it is necessary to approve and disburse on time the budgetary appropriation for undertakings by the regional administration, pursuant to Article 52 (2) (e) of the constitution of the federal Republic of Ethiopia, the regional Government has the power to draw up and administer its own budget.

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት የፌደራል መንግስት እና የክልሎችን □ፉራ ቁጢ □ኦአል እንዲሁም የፌደራሉ መንግስት ለክልሎች የሚሰጠውን ድጎማ በተመለከተ የፌደሬሽንም ም/ቤት የወሰነውን ቀመር መሠረት በማድረ□ □ብሄራዊ □ልላዊ መንግስቱን የ1991 በጀት በይፋ ማወቅ በማስፈለጉ::

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ መንግስት ም/ቤት በክልሉ ሕገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**አንቀጽ 1.** ይህ አዋጅ « የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ መንግስት የ1991 በጀት ዓመት የበጀት አዋጅ ቁጥር 14/1991» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

**አንቀ□ 2.** የብሄራዊ መንግስቱ ሥራዎች ማስፈጸሚያ የተመደበ አጠቃላይ በጀት ከሐምሌ 1/1990 ጀምሮ ሰኔ 30 1991 በሚፈጸመው በአንድ የበጀት ዓመት ጊዜ ውስጥ በክልሉ ከሚገኘው ገቢ ከማዕከላዊ መንግስት ድጎማና ከሌላ ገንዘብ ላይ ከዚህ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ ውስጥ ለተጠቀሱት ሥራዎችና አገልግሎቶች ቀጥሎ እንደተመለከተው::

Whereas, it is necessary to proclaim officially the 1991 fiscal year budget of the Regional Government, pursuant to Artide 62 (7) of the constitution, the Federation, has set the formula to be followed in respect of the sharing of joint revenue as between the federal Government and Regional Governments as well as in respect of subsides too be made to regional Governments by the Federal Government:

Now Therefore, in Accordance with Article 49 of the sub Artide 3 of the Regional constitution. The State council of the Benishangul Gumuz Regional Government hereby prodaimed as follows;

Artide 1. This proclamation b=may be cited as the " 1991 fiscal year budget prodamation of the Benishangul Gumuz Regional Govemment proclamation No, 14/1991 ".

Artide 2. The fiscal year undertakings by the Regional Government is herby appointed for the fiscal year commencing on Hamle 1, 2990 E.c and ending on Sene 30, 1991 E.c from Regional Geovernmtn revenues, Federal Gov;t subsidy and other funds for theunder takings set forth in the schedule hereto:

ሀ) ለመደበኛ ወጪዎች ብር--------------77,994,354

ለ) ለየካፒታል □ች

ብር-------------------------116,991,400

ጠቅላላ ድምር ብር-------194,985,754

( አንድ መቶ ዘጠና አራት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሃበሳ አራት ብር) ወጪ ሆኖ እንዲከፈል በዚህ አዋጅ ተፋቅዷል።

**አንቀጽ 3.** ለፕሮፌሽንና ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች እንደዚሁም ለሥራ ማስኬጃ የተፈቀደው መደበኛ በጀት ወደ ደመወዝና አበል ማዛወር አይቻልም።

**አንቀጽ 4.** ለየካፒታል ግንባታ ሥራዎች ማስፈጸሚያ የተፈቀደውን የካፒታል በጀት ወደ መደበኛ አዛውሮ መጠቀም አይቻልም።

አንቀጽ 5. ለድንገተኛ መጠባበቂያ ከተመደበው በጀት ላይ ክፍያ ሊፈጸም የሚችለው በብሄራዊ □ልላዊ መንግስት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሲወስን ብቻ ነው።

**አንቀጽ 6.** ለቋሚ የክልሉ ሠራተኞች በየወር ሳይቋረጥ የሚከፈል ክፍያዎች አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች የሚሰጠው የደመወዝ ቅድሚያ □ክፊያውን ጊዜ በመወሰን በዚህ ሁኔታ የሚሰጠው ብድር ላይ በዓመት □፪□ ቶ□በ ውስጥ የኢትዮጲያ ብሄረዊ ባንክ በሚያወጣው የወለድ ተመን መሠረት □ንዲጸስ ከፍል ለክልሉ ፋይናንስ ቢሮ ስልጣን ተሰጥቷል።

A) For Recurrent Expenditure

Birr--------------------77, 994,354

B) For Capital Expenditure

Birr----------------------116, 991,400

Grand Total Birr-------194, 985,754

(One Hundred Nine four Million Nine Hundred Eighty five Thosnads Seven Hundred Fifty Four Birr)

Article 3. No Transfers shall be made to appropriations for salaries, wages and allowances from appropriations of the recurrent budget made for professional and other services as well as operational expenditures.

Article 4. No transfer shall be allowed from the capital Budget appropriated to construction works to the Recurrent Budget.

Article 5. Except the approval of the executive committee of the State council of the regional Government, no payment shall be made out of the provision for unforsen expenses.

Article 6. The Regional financial Bureau is here by authorized to grant advance of salary to permanent Regional Civil Servants for necessary cases in accordance with directives issued there on, and to fix the period of repayment thereof and to collect interest thereon at the rate fixed by the National bank of Ethiopia.

□ክፍል 2

የበጀት አስተዳደር

አንቀጽ 7. የብሄራዊ ክልሉ አስፈጻሚ አካላት በጀት የማስተዳደር ሥልጣን

1. ጉዳይ የሚመለከታቸው የብሄራዊ ክልላዊ መንግስት አስፋጻሚ አካላት ሀላፊዎች ለየመ/ቤቶቸው ሥራና አገልግሎት በዚህ አዋጅ መሠረት የተፈቀደላቸውን በጀት የማስተዳደር ሥልጣን አላቸው::

2. አስፋጻሚ አካላት በዚህ አዋጅ የተፈቀደላቸው በጀት ክፍያ እንዲፈጸምላቸው በሚጠይቁ ጊዜ የፋይናንስ ቢሮ ሀላፊ ከብሄራዊ □ልላዊ መንግስት ገቢና ከሌላ ምንጭ እንዲከፍል በዚህ አዋጅ መሠረት ታዟል::

ክፍል ሦስት

ስለበጀት ዝውውር ሥልጣን

አንቀጽ 8. የበጀት ዝውውር ሥልጣን ለሚከተሉት የብሄራዊ ክልሉ አካላት ተሰጥቷል::

ሀ) የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብራሄራዊ ክልላዊ መንግስት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ:-

1. በበጀት ተፈቅዶ በመከናወን ላይ ካለ የካፒታል በጀት በበጀት ዓመቱ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ አርዕስት (ንዑስ አርዕስት) የካፒታል በጀት

**PART II**

**BUDGET ADMINISTRATION**

**Article 7. Powers of the executive Organs of the Regional Government**

1. The Head of the concerned executive organs of the Regional Government hereby authorized to administer the budget out of the amount appropriate here, for the undertakings of their respective organs.

2. The Head of the finance bureau is hereby authorized up on the request of the heads of the concerned executive organs, to disburse out of the Regional Governments Revenue from Federal Government subsidy, and other funds the counts appropriated herein for undertakings of their respective organs.

**PART III**

**BUDGET TRANSFER**

Artide 8. Authorized to transfer budget is vested to the following Regional government organs

(A) Executive committee of the Benishangul /gumuz Regional government State council,

1. From Appropriations of the capital budget for organizing project to anew project head /sub-head is for which budgetary appropriations have not been made.

**2. መደበኛ በጀት ከተፈቀደለት አርዕስት (ንዑስ አርዕስት) በበጀት ዓመት መደበኛ በጀት ላልተፈቀደለት አዲስ አርዕስት (ንዑስ አርዕስት)**

**3. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደ ወደ የካፒታል በጀት፡**

**4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በክልሉ ሥር የሚገኙ ማንኛ ውም የመንግስት መ/ቤት በሥራ ላይ ያውላል መደበኛ ወይም የካፒታል ተራፊ በጀት ወደ ሌሎች ሥራዎች፡፡**

**5. ለመደበኛ በጀት ከተፈቀደው ደመውዝ አበል ወደ ሥራ ማስኬጃ፡፡**

**6. የተፈቀደላቸው ጠቅላላ በጀት መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ በክልሉ መስተዳድር ሥራ ያሉ ሆስፒታሎች ባለፈው በጀት አመት ካስገኙበት ጊዜ ትክክለኛ ገቢ 50% (ሃምሳ በመቶ) ሳይበልጥ ከዘመኑ የበጀት ዓመት ገቢያቸው እንደአስፈላጊነቱ ወጪ እያደረጉ እንዲሰሩበት ለመፍቀድ የፋይናንስ ቢሮ ሀላፊው ሥልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡**

**7. ለመደበኛ በጀት ለአንድ አርዕስት ከተፈቀደው ወደ ሌላ አርዕስት፡**

**8. ከተፈቀደው የካፒታል በጀት ከአንድ አርዕስት (ቢሮ) ወደ ሌላ አርዕስት (ቢሮ) ወይም ከአንድ ቢሮ ፕሮጀክት ወደ ሌላ ቢሮ ፕሮጀክት፡**

**ለ)ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የፋይናንስ ቢሮ ከላይ**

**በአንቀጽ 8 (ሀ) 5 ከተጠቀሰው በስተቀር፡**

2. From appropriation made for head/sub-head of the recurrent budget to a new head/sub-head of the recurrent budget for which budgetary appropriations have not been made

3. From appropriation made for the recurrent budget to capital budget.

4. Whiteout prejudice to Article 1 and 2 of this proclamation, from one Regional Bureau unutilized recurrent and capital budget to other undertakings

5. From appropriations of the recurrent budget made for salaries wages and allowance to operational expenditures.

6. Authority may be delegate to the finance Bureau head to allow regional hospitals to retain and expend within their G. Total budgetary appropriations, receipts from Budgetary the current fiscal year up to an amount not accepts for the provisions fiscal year.

7. From appropriations made for one head to another head recurrent budget.

8. From appropriations made for one head to another head of from appropriations of one bureau project to another bureau project.

(B) Except the provisions of Article 8 sub Article A(5) above, the Benishangul /Gumuz region finance bureau shall have the following budget transfer power.

1. ጉዳይ □የሚመለከታቸው አካላት ሲጠየቁ በአንድ መደበኛ አርዕስት ሥር ከአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላ ንዑስ አርዕስት በየሂሳብ መደቡ

2. ጉዳይ የሚመለከታቸው የክልሉ መንግስት አካልና የፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሲስማሙበት በአንድ የክልሉ መንግስት አካል ሥር በአንድ አርዕስት የክልሉን ወይም በአንድ ንዑስ አርዕስት ወደ ሌላ ንዑስ አርዕስት ወይም ከአንድ ፕሮጀክት ወይም ከአንድ ፕሮጀክት ውስጥ በአንድ ሂሳብ መደብ ሌላ ሂሳብ መደብ፡

3. በመደበኛ በጀት ውስጥ ላለፉት አመታት ግዴታዎች ከተፈቀደው በጀት ወደ ሌሎች አርዕስቶችና ንዑስ አርዕስቶች፡

4. ለመደበኛም ሆነ ለካፒታል ወጪ ተፈቅዶ በሥራ ላይ ያልዋለው ተራፊ በጀት ወደ መንግስት ዕዳ ክፊያ ወይም ወደ ሌላ ወጪዎች።

5.ለኮንስትራክሽን ሥራዎች ለቋሚ መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎች የጠያዘን የካፒታል በጀት ወደ ለሥራ ማስኬጃ ወጪ 8301፡ 8302፡ 8303) ማ□□ር አይፈቀድም።

አሶሳ ታህሳስ 1991
የቢኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት
ያረጋል አይሸሽም
ፕረዚዳንት

1. From appropriations of one sub head of the recurrent budget to another sub head of the recurrent budget within the same head; where requested and the concerned organ.

2. From appropriations made for a head /sub-head project, or item of the capital budget to another head/sub-head, project or item under the same regional organ; where agreed upon by the regional government organ concerned and the Regional Bureau Economic Development.

3. From appropriations under the recurrent budget made for past commitments to other heads and sub heads.

4. From utilized recurrent and capital budget appropriations to public debt payments.

5. No transfers shall be made to appropriations for salaries, wages, allowance and operational expenditure (8330, 8302, 8303) from appropriations of capital goods, machinery's and vehicle

Done at Assosa this December /1998
State council of the

Benishangul /gumuz Regional Government
Yargal Aysheshum
Presidant